# አብዮቱና ትዝታዬ፤ ሌ/ኮ ፍሰሀ ደስታ

***የመጸሃፍ ግምገማ*** ***በታከለ አርጋው***



***ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ላለፈው ግማሽ ምህተ ዓመት  የኢትዮጵያን ሕዝብ በገዙት መንግስታት ውስጥ ቁልፍ በሆነ የስልጣን ስፍራ ተቀምጠው የነበሩ ዓንዳንድ ግለሰቦች ስለዓለፉበት የዐገዛዝ ዘመን በመጽሃፍ ጠርዘው ድሮ ያልነገሩንን ሊንግሩን ተነስተዋል። በዚህ ረገድ አቶ ተስፋዬ ገብረዓብ ፣ ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ዎግደረስ ፣ አቶ ገብሩ አስራት ፣ አቶ ኤርሚያስ ለገሰ ና ሌ/ኮ ፍሰሐ ደስታ ዋንኛውን ስፍራ ይይዛሉ። የግለሰቦቹ አላማ ቢለያይም በአንድ የታሪክ ወቅት ከህዝቡ  ተለይተው በተጻራሪ ጎዳና በመቆማቸው በመሃል መለያየት በመፈጠሩ ህዝብ ያልተረዳላቸው ጉዳዮች አንዳለ ለማስገንዘብ የጓጉ ለመሆናቸው መጻሃፎቻቸው ሲያዝገነዝቡ፤ ሁኔታዎች ከፈቀዱ ግለሰቦቹ በሌላ ዙር የፖለቲካ ትግል ሊገጥሙን ያልደከሙ መሆኑን ከአንዳዶቻቸው እንቅስቃሴ መረዳት ይቻላል። ይህ ካልተቻላቸው ደግሞ ስነ ልቡናችንን ለመግራትና ለመላመድ ይሁን ውይም የንባብ ጥማችንን ለማርካት ገና ብዙ መጻህፍት ለመጻፍ እንዳሰቡ ግለሰቦቹ ያስገነዝባሉ።***

***ይህን አጭር ጽሁፍ ለመጻፍ የተነሳሁበት ዋናው ጉዳይ በቅርቡ ለሕትመትና ለንባብ የበቃው “አብዮቱና ትዝታዬ” የተሰኘው የሌ/ኮ ፍሰሀ ደስታ መጽሐፍ ነው ። መጽሐፉ በ ፲፰ ምሕራፍ የተከፋፈለና ከ፭፻ በላይ ገጾች ያሉት ሆኖ ብዙ ጉዳዮችን የያዘ በመሆኑ እንደ እኔ ላለው ተራ አንባቢ ጠለቅ ያለ ግምገማ ለማድረግ ቀላል አይደለም። ግምገማውን ለማድረግና ሃሳብ እንዳካፍል የገፋፋኝ ጸሃፊው በመጸሃፋቸው ውስጥ ብዙ ክስተቶችና የብዙ ሰዎችን ስሚና ታሪክ ስላነሱ ፣ ብዙ እርስበራሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦች ስለተንጸባረቁና፣ ብዙ በመረጃና በምስክር ያልተደገፉ ክስተቶች ስላነሱ መጽሃፉ በታሪክ መረጃነት ለመቀበል ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ሁኔታዎች በማስተዋሌ ነው። በዚህ ረገድ የታሪክና የፖለቲካ ባለሙያተኞች በበለጠ ምርምር እንዲያደርጉበትና ጸሃፊውም በሕይወት እያሉ መረጃዎቻቸውን ቢጠየቁ መልካም መሆኑን  እግረመንገዴን ለማስገንዘብ ጭምር ነው።***

***“አብዮቱና ትዝታዬ” ኢትዮጵያ ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ጀምሮ በከፍተኛ የፖለቲካ ነውጥ ውስጥ የገባችበትንና በዚህ የፖለቲካ ማዕብል ውስጥ ከመጻህፎቻቸውና በህዝብ ዘንድ ብዙም ድጋፍ ያልነበረው የወታደራዊ ደርግ መንግስት የተጓዘውን ስልጣን የማስከበር የፖለቲካ ጉዞ በመመዝገብ የሚናኝ በመሆኑ ከወገናዊነት ነጻ ሆኖ ሃሳብ ለመስጠትም ሆነ ለመገምገም መቸገሬንም አንባብቢ እንዲያውቅልኝ እጠይቃለሁ።  ስለዝህ ጸሃፊው የዘረዘሯቸውን ትረካዎችን ከመመርመር በመቆጠብ ባጠቃላይ ያስተዋልኳቸውን ፍሬነገሮችና ችግሮች በሚቀጥለው ሁኔታ እገልጻለሁኝ።***

***፩. የመጽሃፉ አጠቃላይ አቀራረብና ይዘት***

***መጽሃፉ ከማህበራዊና ኢኮኖማዊ ሁኔታዎች ይልቅ በበለጠ በፖለቲካዊ ክስተቶች ላይ ያቶኩራል። ከቅድመ የካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም በፊት በየስፍራው በሃገሪቱ የተነሱ ጸረ-መንግስት የገበሬዎች፤ የተማሪዎችና፤ የወታደሮች ፖለቲካዊ ትግል በማተት ለንጉሠ ነገሥቱ ከስልጣን መውረድና ወታደሩ “ሳይወድ በታሪክ ግዴታ” ስልጣን ለመውሰድ የተገደደበትን የመንስዔ ምክኒያቶች በማቅረብ ጸሃፊው ለአብዮቱ ትዝታቸው መንደርደርያ ይሰጣሉ። እነዚህ በቅድመ የካቲት ፲፱፻፷፮***

የተካሄዱ መሰረታዊ የታሪክ ሁኔታዎች ባብዛኛው ጸሃፊው ያልተሳተፉባቸው ሆኖ እያለ ላብዛኞቹ መረጃና ምንጮቻቸውን አለመጥከሳቸው አግባብ ሆኖ አላገኘሁትም። በዚህ ረገድ የመጽሃፉ አሳታሚ ድርጅት ወይም Editor መሟላት የሚገባቸውን መረጃዎች እንዲካተቱ የበኩሉን ሚና መጫወት ይገባው ነበረ። በዚህ የመጽሃፉ መግቢያ ክፍል ጸሃፊው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ላይ ጠንከር ያለ ክሶች ይደረድራሉ ከክስ አልፈውም ለንግስት ዘውዲቱ መሞት ምክኒያት ተጠያቂ መሆንና፤ ልጅ እያሱን በመርዝ እስከ ማስገደል የደረሰ ውንጀላ ይሰነዝሩባቸዋል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ አምባሳደር ዘውዴ ረታ አፈሩን ቀላል ያድርግላቸዉና በቂ መረጃ ትተውልን ስላለፉ ጸሃፊው ክሳቸውን በመረጃ፣ አልያ አንባቢውን ወደ አምባሳደር ዘውዴ ረታ መጽሃፎች ቢጠቁሙት ከበሬታ ያተርፉ ነበረ ።

በቀሩት ፲፬ ምህራፎች ጸሃፊው በ፲፱፻፷፮ ዓም በፈነዳው አብዮት ውስጥ የወታደሩ ስብስብ ደርግ እንዴት የመንግስት ስልጣን ኮርቻ ላይ እንደወጣ አብራርቶ በበቂ መረጃ ከሞላጎደል ያቀርባል። በተጨማሪ የመንግስት ስልጣንን፣ ተደማጭነትንና ፣የፖለቲካ የበላይነትን ለመቅዳጀት በደርግ አባላት ውስጥ ፤ በደርግና ከመንግስት ኔትዎርክ ውጭ በተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ፤ ጊዜው አፍርቷቸው በነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የተደረገውን ትንቅንቅ ፤ ጭካኔና ፤ ተንኮል የተሞላበትን የፖለቲካና የመሳርያ ትግል ትልቅ ታሪካዊ ድራማ ወይም ተውኔት ሊወጣው በሚችል መልኩ ተብራርትዋል። የጽሃፊውንም የማስታወስ ችሎታ ያደንቋል።

፪. በታሪክ መረጃነታቸው የሚያገለግሉ መረጃዎች

ሀ) በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም አብዮቱ እንዴት እንደተነሳ ፤ የወታደሩ ኪፍል አብዮቱን ለማቀጣጠል ያበረከተውን አስተዋጽዖና ህዝቡም በየስፍራውለብዙ አመታት ሲፈራ የነበረውን የፊውዳል ስርዓት ለመጣል መንቀሳቀሱን ጸሃፊው አብራርተዋል።ከዚህ በተጨማሪ መጸሃፉ ከመዘገባቸው ክስተቶች ዋነኛ ሊተኮርበት የሚገባ ቢኖር ግለሰቦች በታሪክ ውስጥ የሚጫወቱትን ትልቅ ሚና ነው ። መጸሃፉ እንደሚያሳየው ኮ/ል መንግስቱ ሃይለ ማሪያም ለ ፲፯ ዓመታት ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የነበሩትን የደርግ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕርግ ወታደሮች ፤ ከፍተኛ የፖለቲክ ንቃትና የውጭ መንግስት ድጋፍ የነበራቸውን የሕዝብ ድርጅት ጽህፈት ቤት አባላትን ፤በመንግስት ውስጥ ያገለግሉ የነበሩ የተማሩና ልምድ ያካበቱ የሲቪል ሰራተኞችን፤ የጦር አለቆችን በሙሉ በውዴታም ሆነ በግዴታ ተቆጣጥረው ሃገሪቷን ለ፲፯ ዓመታት መግዛት መቻላቸው እራሱን የቻለ ምርምር የሚጠየቅ የሃገሪቱ የታሪክ ገጠመኝ ነው ማለት ይቻላል። ጸሃፊው ክስተቶችን በሪፖርት መለክ ከማቅርብ ውጭ ኮ/ል መንግስቱ የተጠቅሙብትን ስልቶችና ዘዴዎች ባለማብራራታቸው ጉዳዩ ሌላ መጽሃፍ የሚዎጣው ታሪክ ይሆናል። ከሃገሪቱ ታሪክም እንደምንረዳው የቀድሞ መሪዎች ሰዎችን በጋብቻ፣ በርስትና ፣ በሹመት ደልለው በመያዝ ሲገዙ የኮ/ል መንግስቱ ዘዴ ምን እንደነበረ ማወቁ ለህዝብ የመብትና የነጻነት ትግልና ከአምባገነኖች ጋር ለሚደርግ ትግል ቅድሚያ ዝግጅት ትምህርት ይኖረዋል። ይህ የአንድ ሰው አምባገነንት በታሪካችን እስከ አሁን ድረስ እየተደጋገመ በመከሰቱ ችላ የማንለውና ትክረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ።

ለ) ሌላው ታሪካዊ ክስተት ወታደራዊውን መንግስት በመቃወም የፖለቲካ ስልጣንን ከደርግ እጅ ለመንጠቅ የተነሳው የፖለቲካ ድርጅት ኢህአፓ ጉዳይ ሲሆን፤ ይህ ድርጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ በመደራጀት በቂ ፖለቲካዊ፣ ድርጅታዊና፣ ኢኮኖሚያዊ የበላይነት የነበረውን

*ወታደራዊ መንግስት ደርግን ጥሎ ስልጣን ለመውሰድ ተቃርቦ እንደነበረ የኮ/ል ፌስሃ መጸሃፍ ያሳያል። ጸሃፊው ስለዚህ ድርጅት ከሚገባው በላይ ብዙ ቦታዎች ላይ ያነሳሉ፤ ለብዙ ችግሮችና ውድቀቶች መንስዔ መሆኑንም በምሬት ያወሳሉ ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ብዙ ጸሃፊዎች ችላ የሚሉት ኮ/ል ፍሰሃ ግን በመጸሃፋቸው ያሰፈሩት ታሪካው ሁኔታ አንዱ ብአብዮቱ መባቻ ላይ ስለነበርው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው። ተማሪዎቹ ትግላቸውን ቅርጽ ለመስጠት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ድርጅት በማቋቋም በአብዮቱ ውስጥ አስተዋጽዖ ለማድረግ መሞከራቸውታሪካዊ ነው።ተማሪዎቹ ይበልጥ እየነቁና እየተደራጁ ሲመጡ ድርጅታቸውን የኢትዮጵያ አብዮታው ወጣቶች ሊግ(ኢወአሊ) ብለው በመሰየም በትግሉ ውስጥ ተሳትፎቸውን ቢቀጥሉም በማሃሉ ይህ የተማሪዎች ድሪጅት በኢህአፓ በመጠለፉ የወጣቱን ታሪክ በሚያጎድፍ የግድያና የሽብር ተግባር ፈጻሚ ሆኗል ሲሉ ጸሃፊው ስለዚህ ድርጂት ብዙ ያስንብቡናል።*

## ሐ) *በ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም የደርግ ኢሠፓ መንግስትን ለመገልበጥ የተደረገ የመፈንቅለ መንግስት መከራ*

*እንደሚታወቀው በመፈንቅለ መንግስቱ መከራ የተሳተፉት ግለሰቦች የጠለቀ የፖለቲካ የውትድርናን የጸጥታ መቆ ጣጠር ልምዶች እያላቸው እንዴት መከራው ሊከሽፍ እንደቻለ ለብዙ ስዎች እንቆቅልሽ ነበረ።ለዚህ ጥያቄ መልስ የሻምበል ፍቅረ ስላሴ ዎግደረስ መጸሃፍ "እኛና አብዮቱ" አንዳች ቃል ሳይተነፍስ ለህትመት መብቃቱ የብዙ ሰዎች ቅሬታ ነበር። ይህን በተመለከተ ከኮ/ል ፍሰሃ ብዙ ጠብቄ ነበረ። መጽሃፉን ካነበብኩ በኋላ ግን ጸሃፊው ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጪ ሊሆኑ እንደማይገባ ማስተዋል ችያለሁኝ። ምክኒያቱም ጸሃፊው ካቀረቡልን መራጃ አንብቤ እንደተርዳሁት ኮ/ል ፍሰሃ ደስታ ለኮ/ል መንግስቱ ሃይለማሪያም በጣም ታማኝ መሆናቸው ዋናው ቁምነገር ሲሆን ። በመጽሃፉ ውስጥ በግልጽ እንደሰፈረው ከሆነ ከመንግስት ደህንነት ሃላፊው ቀጥሎ ከማንም በፊት ስለ ዱለታው እውን መሆን በመጀመሪያ መረጃ የደረስው ለ ኮ/ል ፍሰሃ ነው። መረጃው እንደደረሳቸውም ጉዳዩን ለ ኮ/ል መንግስቱ መንገሩ የራሳቸውን የስለላ መረብ ማስመታት ስለሆነ መንግስቱ ሃገር ከለቀቁ በኋላ ጸሃፊው ኩዴታውን ለማክሸፍ በሚቻላቸው ተንቀሳቅሰዋል ። ለዚህ ተግባር እውን መሆን የራሳቸው የቅርብ ረዳት ዱለታው ይካሄድ ከነበረበት ስፍራ ሆነ መራጃ ይሰድላቸው ነበር ፤ እራሳቸውም ከሌሎች የመንግስቱ ሃይለማሪያም ወዳጆች ጋር በመሆን ሬድዮና መገናኛን ተቆጣጥረው፣ የክብር ዘቡን አንቅሳቅሰው ፣ የቤተመንግስቱን ልዩ የጸጥታ ጠባቂዎች አሰልፈው መንግስታቸውን ለጊዜውም ቢሆን ከውድቅት አድነዋል። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ጸሃፊው አንድ ምዕራፍ ከፍተው "መፈንቅለ መንግስቱ ለምን ከሸፈ?" በማለት ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል እንደሚባልው ተረት ለጥያቄው መልስ ለመሻት መሞከራቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ጸሐፊው በዚህ ጉዳይ ላይና በየዓምዱ የሚያቀርቡት አንዳንድ መረጃዎች ግለሰቡ እራሳቸው ጠንካራ የሆነ የግል ወይም ከሌሎች ጋር (በgroup)የደህንነት መረብ እንደነበራቸው ከአተራርካቸው መረዳት ይቻላል። ለዚህም ልሆን ይችላል በወቅቱ የደህንነት ሚኒስተር ከነበሩት ከኮ/ል ተስፋዬ ወልደሥላሴ ጋር የሻከረ ግኑኝነት የነበራቸው ምሆኑንና ሁለታቸውም የኮ/ል መንግስቱን ስነልቦና ለመቆጣጠርና አዎንቷ ለማግኘት ይራኮቱ የነበረ መሆኑን የሚያመላክቱ ሃሳቦችን ጸሐፊው የሚያንሸራሽሩት።*

፫. የተዛቡ አመለካከቶችና ስህተቶች

ጽሐፊው ብዙ እራሳቸው በአካል ያልተገኙበትን ክስተቶች ሲዘግቡ በስፍራውና በውቅቱ የነበሩ ሰዎችን በዋቤነት ሳይጠቅሱ፤ ውይም መረጃዎቹን ከየትና ከማን እንዳገኙ ሳይጠቁሙ ፤ ዝርዝር ሃተታ ባንዳንድ ዋና ዋና ነገሮች ላይ ማቅረባቸው መጽሐፉ በታሪክ ዘጋቢነቱ ልያገኝ የሚገባውን ዋጋ ያሳንሳል። በማያያዝ ከዚህ ከጥሎ የምዘረዝራቸው የጸሃፊው ዘገባዎች ለዚህ ግንዛብዬ መረጃ ናቸው፦

ሀ ) በትግራይ ተወላጆችና በሌሎችም ጭምር በአጼ ሀይለ ሥላሴ ዘመን የተለየ በደል ተፈጽምዋል የሚል አቋም ጸሀፊው መጥቀሳቸው፦

በዚህ ጉዳይ ጸሃፊው በትግራይ ተወላጆች ላይ ሆን ተብሎ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ጥቃት ይፈጸም እንደነበረ፤ በደርግ መንግስት ውስጥና በመንግስት መስርያቤቶች በነበሩ የትግራይ ትወላጆች ባለስልጣናት ላይ ክትትል ይደርግ እንደነበር አልፈው አልፈው በመጸሃፋቸው ውስጥ ያወሳሉ። ነገሩ አልተፈጸመም ብሎ ለመከራከር ባይቻልም  በጣም ለማመን ያስቸገረኝ ግን ንጉሰ ነገስቱ በትግራይ ህዝብ ላይ ይፈጽሙት ነበረ ለሚሉት አቤቱታ ጸሃፊው የግል ገጠመኛቸውን የተረኩበት ሁኔታ ነው። በዚህ ገጠመኛቸው መሠረት ጸሐፊው የ፲፬ ዓመትና የ፰ኛ ክፍል ተማሪ ሆነው ሳለ በትምህርት ቤት መማርያ ክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል በተንሳ ረብሻ ተማሪዎቹ ንጉሰ ነገስቱ ፊት መቅረባቸውን ይጠቅሱና በማስከተል ንጉሱ ስብሕና የሚያጎድፍ ስድብ፣ እስራትና፣ ድብደባ በግል እንደደረስባቸውና ሌሎች ቁጥራቸው ፲፭ የሚደርስ ተማሪዎች ደግሞ ከትምህርት ገበታቸው መባረራቸውን ብምሬት ያስታውሳሉ። ነገሩ ተከስቶ ከሆነ በጣም የሚያሳዝንና ከአንድ ንጉስና መሪ የምይጠበቅ ሲሆን ፤ ነገር ግን ጸሃፊው በጊዜው በደል ከደረሰባቸው መካክል የጥቅቶቹን ስም ለዋቤነት ብጠቅሱ መልካም በሆነ ነበረ።

ለ) ፍትህና ሕግ እንዲከበር ያለመጣር

ጽሀፊው በተለያየ የመጽሃፉ ክፍሎች ህገ-ወጥ ተግባራትን ያነሱና ድርጊቶችን ማን እንደፈጸመው እንደሚያውቁና እውነትነት እንዳለው ልማስረዳት ሕገ ወጥ ተግባራቱን ከፈጸሙ ግለሰቦች ከራሳቸው አንደበት ነው የሰማሁት፤ እከሌ ነው የነገረኝ ፤ ለደህንንቱ ስል ስሙን አልጠቅስም፤ ...ወዘተ እያሉ ሲጽፉ ወይም የግርጌ ማስታወሻ እየስጡ ሲያስረዱ ይስተዋላል። በዚህ ረገድ አንዳንድ ግለሰቦች የሰው ህይወት እስከ ማጥፋት የደረሱበት አጋጣሚ እንደነበረም ይተረካሉ። ለምሳሌ ብ ፲፱፷፪ ዓ.ም የቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፕሬዝዳንት ተማሪ ጥላሁን ግዛው የተገደለው ቀደም ሲል በክብር ዘበኛ ውስጥ ጸሃፊው በውትድርና ሙያ ያሰለጠንዋቸውና የሚያውቋቸው ሁለት ወታደሮች እንደሆኑና ጊዜው ካለፈ በኋላ ሁለቱም ድርጊታቸውን ለጸሃፊው እንዳመኑላቸውና ይጠቅሳሉ። በማስከተልም  ለደህንነታቸው ሲሉ ስማቸውን ይፋ እንዳላረጉ ያስረዳሉ። ይህ ጉዳይ በህግ አንጻር ሲታይ  ጸሃፊው የወሰዱት አቋም ትክክል አይደለም። ከመኰንንነት ተነስተው እስከ ሃገሪትዋ ምክትል ፕሬዝዳንትነት የደረሱት ጸሃፊው ያላስከበሩት ፍትህ ማን ሊያስከብረው ይችላል ?

ሐ) ይቅርታ ስለመጠየቅ

ኮ/ል ፍስሀ ደስታ በመጸሃፋቸው ሽፋን፣ በመግብያና በማጠቃለያ ክፍሎች ውስጥ “በማወቅ በድፍረት፣ ባለማወቅ ብስ ህተት፣” ለፈጸሙት ሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ ይላሉ። ነገር ግን መጽሃፉ ውስጥ ሲገባ ጸሃፊው በተደረጉት ስህተቶች ብመጸጸት እርሳቸውም ሆኑ ጓደኞቻቸው የፈጸሙት ስህተት ምን እንደሆነ ከመጠቆም ይልቅ ለስህተቱ በተጠያቂነት ለሎችን ሲከሱና ምክኒያቶች  ሲሹ ይስትዋላሉ። ለምሳሌ በ አብዮቱ መባቻ ላይ ስድሳ የቀድሞ መንግስት ባለስልጣናትና ባለሌላ ማዕረጎች በደርግ አባላት ውሳኔና ትዕዛዝ በጥይት ተረሽነው እንዲገደሉ ውሳኔ ሲተላለፍ ጸሃፊው በስራ ምክኒያት በስፍራው አልነበርኩምና ከደሙ ንጽሕ ነኝ ፣ ግድያው አግባብ አይደለም ይሉና በማስከተል “ሆኖም ግን አንዳንዶቹ ባለስልጣናት በህዝብ ላይ የተለያየ በደልና ሰቆቃ ያደረሱ፤ የንጉሱን ተቃዋሚዎች የገደሉ፤ በአደባባይ ሬሳ የሰቀሉ …ወዘተ” በማለት የይቅርታ አድርጉልኝ ጥያቄው ይረሳና ለግድያው ምክኒያትና መንስሄ በመፍጠር የመከላከያ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ። በተጨማሪ ኮ/ል መንግስቱ ሃይለማርያም በ፲፱፻፷፱ ዓም በ ኢህአፓ አባልነት ጠርጥረው የገደሏቸውን እነ ጄነራል ተፈሪ በንቲንና ሌሎች ፯ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረግ የደርግ አባላትና ወታደሮች በተመለከተ ጸሃፊው በድርጊቱ ያዘኑ ቢሆንም ሟቾቹ ከእነ ቤተስቦቻቸው ሳይቀር የኢህአፓ ኣባላት መሆናቸውንና ተንኮል የተሞላባቸው ድሪጊቶች የፈጸሙ ናቸው ይሉና። “ኮ/ል መንግስቱ አስቀድሞ እርምጃ ባይወስድ ኖሮ የከፋ ጉዳት የደርስ ነበር” በማለት ድርጊቱን ከማውገዝና በነገሩ መጸጸታቸውን ከመናገር ይልቅ ለግድያው መከላከያ ፍልጋ ይዋትታሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ብ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በከፍተኛ ማዕረግ ላይ በነበሩ ጄነራሎች የተሞከረውን መፈንቅለ መንግስት ጸሃፊው እራሳቸው ካከሸፉና ለ፳፫ ጄነራሎች ህይወት መጥፋት ምክኒያት መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከማዘንና ከመጸጸት ይልቅ አንዳንዶቹን ጄነራሎች  ጸሃፊው የተለያየ ጸባየ-ብልሹ ይሆኑ ባህሪያት የነበራቸው ናቸው ይሉናል።ከ/ኮል መንግስቱ ሃይለማሪያም ጋር ሲያወዳድሯቸውም ጄነራሎቹ ለሃገሪቱ የነበራቸው ተመኔታ በጣም አናሳ እንደሆነ ይገልጻሉ።በኩዴታው መክሸፍ አንዳንድ ሰዎች አንደሚሉት ሃገሪቷ እንዳልተጎዳች ጸሃፍው ይነግሩናል። በጄነራሎቹ ላይ የተወሰደውንም የመጨረሻ  እርምጃ እንድህ ሲሉ የደግፋሉ፦ “የጠላትና የሰራዊቱን ሁኔታ ሳይገመግሙ ያካሄዱት መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሀገራቸውን ጎድተው ሠራዊቱን ለውድቀት ሀገሪቱም አሁን ለደረሰችበት ሁኔታ ተጠያቂ ናቸው” ። በማለት በግድያው ማዘን ሳይሆን ይቅርታ የጎደለው የድመዳሜ ሀሳብ ይሰጣሉ።

በየአደባባዩ ጎራ ለይተው ለተፋለሙት ጸሃፊው “ጥፋቱ የሁላችንም ነውና” ሃላፊነቱን እንጋራ የሚል ስሜት ያንጸባርቃሉ።  “ደርግ እንደማንኛውም አብዮት ያካሄዱ ሃገራት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ነበሩት……. የተካሄዱትም ሽብሮች የሚወደሱና የሚያስደስቱ ባይሆንም እያንዳንዱ አብዮት የራሱ ይሆነ መቅሰፍት አለው” ልንረዳቹ አንችልም የሚል ማርክሳዊ ትንታኔ ሰጥተው፤  ባይሆን “ኑና ቁጭ ብለን እንወያይ…. የጋራ መድርክ እንክፈት” በማለት አስታራቂም ሳይሹ ሌላ ዕድል እንዲሰጣቸው የግርጌ ማስታወሻ የሰጣሉ።

፬. ጸሃፊው ሳይዘግቡ ያለፏቸው ዓበይት ክስተቶች

ጸሃፊው ከነበራቸው ልምድና የስራ ሃላፊነት የተነሳ ብዙ ጉዳዮችንና ክስተቶችን ማወቃቸውን በመጻሃፋቸው ውስጥ ባሰፈሯቸው ዓበይት ጉዳዮች መረዳት ይቻላል። ነገር ግን በሚቀጥሉት ጉዳዮች ላይ የሚያውቁትን ቢሉ የተገባ ነበር እላለሁኝ፦

ሀ) የሃውዜን እልቂት

ጸሃፊው ስልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት በትግራይ ውስጥ ብወያኔና በኢትዮጵያ ሰራዊት መካከል ብዙ ውግያ ተካሂዳል፤ በመጻሀፉም ውስጥ በሰፊው ታትቷል። ነገር ግን በ ፲፱፻፹ ዓ.ም ሰኔ ወር በሃወዜን ከተማ በጦር አውሮፕላኖችና በሄልኮፕተር የታገዘ የቦንብ ድብደባ ብመንግስት ወታደሮች አንደ ተፈጸመና ብዙ ስዎች እንደተገደሉ፤ ወያኔ ደግሞ ድርጊቱ ኢንዲፈጸም ራሱ የተጫወታቸው ሚናዎች እንደነበሩ ለህዝብ ግልጽ ያልሆነ መራጃ ሲናፈስ ዓመታት ተኮጥረዋል። ጸሃፊው በትግራይ ውስጥ ስለተካሀዱ የፖለቲካም ሆነ የጦርነት ኪስተቶች ምዕራፍ ሰጥተው ሲዘግቡ የሃውዜኑን እልቅት ለምን ችላ አንዳሉት አጠያያቂ ነው።

ለ) እኛና አብዮቱ የሻምበል ፍቅረ ስላሴ መጸሃፍ

ኮ/ል ፍሰሃ ደስታ መጽሃፋቸውን ከማሳተማቸው በፊት በደርግ ውስጥና በኋላም በኢሰፓ ጎን ለጎን አብረው የትጓዙትና፤ ወያኔም ስልጣን ስይዝ የእስርቤት ጓዳቸው የነበሩት ፍቅረ ስላሴ ዎግደረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ አብዮቱና የፖለቲካ ሂደቱ ጽፈዋል። ነገር ግን ኮ/ል ፍሰሃ ስለዚህ መጸሃፍ አንዳችም ቃል ሳይተነፍሱ ወይም በዋቤነት ስይጠቅሱ ማለፋቸው የሁልቱንም መጽሃፍት በታሪክ የምይዙትን ስፍራ ዋጋ ያሳንሳል። በዚህ ረገድ አሳታሚው ውይም ኤዲተሩ(Editor) ስሕተት ፈጽሟል።

በመጨረሻ መጽሀፉ ባጠቅላይ ኢትዮጵያን በአንድ የታሪክ ወቅት የገጠማትን ፈተናና የወደፊት ህልውናዋን የወሰነ የፖለቲካ ጉዞ ዘግቧል። ለአብዛኞቻችን በአብዮቱ ውስጥ ላለፍን መጽሃፍ ከሞላ ጎደል ታሪካችንን የዘገበ ማህደር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ኢትዮጵያውያን በራሳችን ላይ ዓምጸን ፤ ሃገሪቱን በጥፋት ስደድ አጋይተንና ለጅብ ስጥተን፤ ከታሪክ ተጠያቂነት ለመዳን ፈረንጆቹ እንደሚሉት ፲፩ ኛው ሰዓት ደርሶ በመቻኮል ላይ መሆናችንን ከመጽሃፉ መገንዘብ ይቻላል። ጸሃፊው የፖለቲካ ሰው ስለ ነብሩና በዚህ የታሪክ ጉዞ ላይ መዳፋቸውን አሳርፈው ስለ ነበረ ብዙ ጥያቄዎች ቢነሳባቸው የሚግርም አይሆንም። ሃላፊነት ተስምቷቸው ጊዝያቸውን ወስደው በመጻፍ ለትውለድ የሚተላለፍ መረጃ በመተዋቸው ምስጋና ሊቸሩ ይገባል።

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
November 21, 2015